ወንጌል፡ ተጋብዛቹሓል!

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ሉቃስ 14:15-24

ኢየሱስም፣ “አንድ ሰው ታላቅ ግብዣ አዘጋጅቶ ብዙ እንግዶችን ጠራ” ሲል መለሰለት።

—ሉቃስ 14:16

ስለ ወንጌል ማሰብ የክርስትና እምነት ማእከላዊነትና ሕይወትን የሚቀይር የደስታ መልእክት እንደሆነ ያስታውሰናል። ለዚህ ነው ይህን ምሳሌ በጣም የምወደው፤ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያለውን ሕይወት ለመግለጽ ኃይለኛ ዘይቤን ይጠቀማል፡ ታላቅ ግብዣ።

በኢየሱስ ዘመን፣ ግብዣዎች ብዙውን ጊዜ በማኅበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶች ለማሰብ እና ለማክበር ይውሉ ነበር። እንዲያውም የኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምር የተከናወነው በሠርግ ግብዣ ላይ ነው። የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ ቤተሰቡን ከማህበራዊ ኀፍረት ለማዳን፣ ኢየሱስ ብዙ ማሰሮዎችን ወደ ወይን ጠጅ ለወጠ (ዮሐንስ 2፡1-11)።

በሉቃስ 14 ላይ፣ ኢየሱስ ለወዳጆቹ ግብዣ ስላዘጋጀ ስለ አንድ ሀብታም ሰው ታሪክ ይናገራል። ሁሉም የመጀመሪያውን ግብዣ ተቀብለዋል፤ ነገር ግን የግብዣው ቀን ሲመጣ እና ምግቡ ዝግጁ እንደሆነ ሲነገራቸው አጥጋቢ ያልሆነ ሰበብ ይሰጣሉ የጋባዡን ልግስናም አልተቀበሉም። በዚህ የተናደደ እና የተበሳጨው ጋባዥ ለመምጣት ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ድግሱን ክፍት ያደርገዋል።

ይህ እንድንደሰት የተጋበዝንበት የመንግሥቱ ሕይወት ሥዕል ያሳየናል። አንዳንድ ጊዜ ይህ ምሳሌ “እግዚአብሔር ድግስ ዘዘጋጅቷል፣ እየመጣህ ነው?” በሚል መልኩ ይጠቃለላል። ወድጄዋለሁ! ይህ ለእኔ ጥሩ ዜና ይመስላል!

ይህ ዓለም ከሚያቀርበው ከማንኛውም ነገር በኢየሱስ ያለው ሕይወት የተሻለ እና የበለጠ አስደሳች እንደሆነ ለማየት ፈቃደኛ ነኝ? ሁሉንም ነገር ጥዬ ወደ በዓሉ ለመሮጥ ዝግጁ ነኝ?

አባት ሆይ፣ በመንግሥትህ ውስጥ ያለው ሕይወት ለዘላለም የምንደሰትበት ታላቅ በዓል መሆኑን እንዳየው እርዳኝ። በህይወቴ ውስጥ በሌሎች ነገሮች ትኩረቴ እንዳይወሰድ ለከበረው ለግብዣክም ዛሬ ምላሽ እንድሰጥ ጸጋህ ያግዘኝ። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ጽሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ወንጌል፡- ሥር ነቀል ለውጥ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ሮሜ 6፡1-11

ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን፤ — ሮሜ 6:8

ስለ ጌታችን መልካም ዜና፣ ወንጌል ስናስብ፣ በሕይወታችን ላይ ስለሚያመጣው ሥር ነቀል ለውጥ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ከጥቂት አመታት በፊት፣ በቅርቡ ከኢራን የመጣችውን አቫን የማጠመቅ እድል ነበረኝ። ጉዞዋን የጀመረችው ጎረቤቷ የቤተክርስቲያናችን አባል ክርስቲያን መሆኗን ባወቀች ጊዜ ነው። አቫ ብዙ ጥያቄዎች ነበሯት፣ ይህም ለብዙ ወራት አንድ ለአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አደረግን፣ በዚህ ጊዜ አቫ በአእምሮዋ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ነገር ለመጠየቅ ነጻነት እንዲሰማት እናደርግ ነበር። በኋላም የሴቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድንን ተቀላቀለች፣ በመጨረሻም አቫ ኢየሱስን እንደ አዳኛዋ ተቀበለች ህይወቷንም እሱን ለመከተል ሰጠች።

የዚህን ወቅት ሽግግር ለማመልከት፣ አቫ መጠመቅ ፈለገች። በሮሜ 6 ላይ እንደተገለጸው በጥምቀት ውሃ ውስጥ ለመጠመቅ ትፈልጋለች፣ እና ብዙ ሰዎች ሲሰበሰቡ ስለምትፈራ ትንሽ ሰው በተገኘበት እንዲሆን ጠየቀች። ስለዚህ በሚያምር እሮብ ጠዋት፣ ወደ 15 የሚጠጉ ሴቶች በአጎራባች ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ተሰብስበው፣ የአቫን ጥምቀት - በኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ ተሳትፎዋን አከበርን። እንዴት ያለ ቀን ነበር!

የእምነት ጉዞህ ምንም ይሁን ምን፣ ይህ የወንጌል ልብ ነው፡ እምነታችንን እና መደገፋችንን በኢየሱስ ላይ በማድረግ፣ ለአሮጌው ሰውነታችን እንሞታለን እናም በእርሱ ለ አዲሱ ህይወት እንነሳለን—ከአሁን ጀምሮ እና ወደ ዘላለም እንኼዳለን። ዛሬ እራሳችሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ ህያው አድርጋችሁ ቁጠሩ!

አባት ሆይ፣ በአንተ ሞትና ትንሳኤ፣ እኛም ለአዲስ ሕይወት መነሣት ስለቻልን እናመሰግንሃለን። በህይወታችን ውስጥ በሚያጋጥሙን ሁኔታዎች ሁሉ ዛሬ በአንተ ላይ እምነት እንድንጥል እርዳን። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ጽሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ወንጌል፡ ተወዳቹሓል!

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — 1 ዮሐንስ 4: 7-12

ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም። — 1 ዮሐንስ 4: 10

ባለቤቴ የክርስቲያን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪ ነች። አንድ ቀን ተማሪዎቿን "ኢየሱስ ይወደኛል…" የሚለውን ዓረፍተ ነገር እንዲያጠናቅቁ ጠየቀቻቸው። ሁሉም ተማሪ ማለት ይቻላል እንደ "አንዳንድ ጊዜ ለእህቴ ደግ ስለምሆን" ወይም "በትምህርት ቤት የተቻለኝን ለማድረግ ስለምሞክር" በሚሉት ሀረጎች መለሱ።

ሁሉም ተማሪ ማለት ይቻላል የኢየሱስን ፍቅር ለማግኘት ካደረጉት ጥረት ጋር ማገናኘቱን መስማት አስደሳች ነበር። ይህ ሀሳብ ከየት መጣ? የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት አይደለም ወንጌልም አይደለም። እውነተኛው የወንጌል ልብ በ1ኛ ዮሐንስ 4:10 "ፍቅር ይህ ነው፤ እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም የሚለው ነው።

የወንጌል መልእክት እኛ ኢየሱስ እንዲወደን ማድረግ የምንችለው ምንም ነገር እንደሌለ ነው። መዳናችን ሙሉ በሙሉ ነፃ፣ ያልተገባ ስጦታ ሆኖ ቀርቧል፡ በቀላሉ እንቀበላለን። ምንባባችን ሁሉንም በአንድ ቃል ያጠቃልላል፡ ፍቅር።

ዛሬ ምሥራቹን ተቀበሉ፡ ይህ ፍቅር ነው፤ እግዚአብሔርን እንደ ወደዳችሁ (ወይም የእግዚአብሔርን ሞገስ ለማግኘት ሌላ ነገር እንዳደረጋችሁ) አይደለም፤ ነገር ግን የተወደዳችሁት እርሱ ስለወዳችሁና ልጁን ስለ ኃጢአታችሁ የድህነት መስዋዕት አድርጎ ስለ ላከ ብቻ ነው። አኛ እኛ ነን እግዚአብሔር ግን ፍቅር ነው።

አምላክ ሆይ፣ ፍቅርህ የሁሉም ነገር መነሻ እንደሆነ እንዳስታውስ፣ ኢየሱስን ለእኔ ያለህ ታላቅ የፍቅር ስጦታ አድርጌ እንድቀበል እርዳኝ። በምላሹም እንድወድህ እርዳኝ። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ**[https://todaydevotional.com/](https://todaydevotional.com/)** ጽሑፈ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ታላቅ አምላክ፤ ታላቅ ተልዕኮ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — መዝሙር 96: 1-13

ክብሩን ለአሕዛብ ተኣምራቱንም ለወገኖች ሁሉ ንገሩ፤ —መዝሙር 96:3

በቅርቡ ወጣቱ የልጅ ልጃችን በአልጋው ላይ በጸጥታ ተኝቷል። በድንገት አንድ ጥያቄ አነሳ:- "እማዬ፣ ሁሉንም ነገር የፈጠረው አምላክ ከሆነ፣ ታዲያ አምላክን ማን ፈጠረው?"

እንዴት ያለ ጥሩ ጥያቄ ነው! እና እግዚአብሔር ምን ያህል ትልቅ ነው?

መዝሙር 96 የአጽናፈ ዓለሙን አምላክ እንደምናገለግል ያስታውሰናል። የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን መጠን ሰማይንና ምድርን ብቻ ሳይሆን የሕይወታችንን ዝርዝር ሁኔታ ከሚያውቅ ከታላቁ እና አስደናቂው አምላካችን ጋር ሕይወት ሰጪ ግንኙነት ውስጥ ገብተናል። ይህ ከእኛ የሚበልጥ ታሪክ አካል ያደርገናል።

እኛ በሁሉም የአለም ማዕዘናት የእግዚአብሔርን ተልእኮ የምትኖረው የአለም አቀፍ ቤተክርስትያን አካል ነን። በመዝሙር 96:3 ላይ "ክብሩን ለአሕዛብ ተአምራቱንም ለሕዝቦች ሁሉ ንገሩ" የሚለው ይህን ታላቅ ተልእኮ እና የቤተክርስቲያንን ስራ በሚያምር ሁኔታ ያሳያል።

በዚህ ወር የዚህ ትልቅ ታሪክ አካል መሆን ምን ማለት እንደሆነ እንመረምራለን። የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራዎች ታላቅነት በህይወታችን ማወጅ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት አራት ቁልፍ ቃላትን እንጠቀማለን፡ ወንጌል፣ ምስክር፣ ሁለንተናዊ እና ብዝሃ-ባህል። የምናመልከው ታላቅ አምላክ ነው ይህ አምላክ ደግሞ ታላቅ ተልእኮ እንዳለው ነግሮናል ይህ ተልእኮ ስሙን በአህዛብ ሁሉ መካከል የማሳወቅ እና እርሱን የመወደስ ነው።

በምድራችን ዙሪያ ሁሉ ስሙ ባልተጠራባቸው የሕዝብ ክፍሎች መካከል እርሱን ለማሳውቅ እንደ ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ቤተክርስቲያን እና የክርስቲያን ማህበረሰብ በመያያዝ በጸሎት፣ በጥናት ፣ በመሄድ እና በመቀበል ልንዘረጋ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ለበረት የምንሆን ሕዝቦቹ ያድርገን።

እግዚአብሔር ሆይ፣ ከሁሉም በላይ ጌታ ነህና እናመሰግንሃለን፣ ስለአስደናቂው፣ አለምአቀፍ ተልእኮህ እናመሰግንሃለን። በእያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍል አንተን ማንጸባረቅ ምን ማለት እንደሆነ እንድንማር ልባችን ክፍት ይሁን። ኣሜን።

በኬቨን ድራፍ የተጻፈ ከ[https://todaydevotional.com/](https://todaydevotional.com/) ጽሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ